ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)

ህዳር 2013 — የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች — ቁጥር 39

# ሉላዊነት፣ ስፋፊ የእርሻ ኢንቨስትመንቶች እና የአካባቢው ነዋሪዎች ምላሽ በምዕራብ ኢትዮጵያ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን የሚያካሂድ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

♣ ♣ ♣

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ኃብዞ ያወያያል።

♣ ♣ ♣

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፤ በልማት ዙሪያ ውይይቶችንም ያካሂዳል።

♣ ♣ ♣

በርዕሱ ዙሪያ ኃሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜል አድራሻችን ላኩልን።

♣ ♣ ♣

ኢሜል፡ fss@ethionet.et

## መግቢያ

በካፒታሊዝም ዘዴ የምርትና ፍጆታ ማስፋፊያ ተብሎ ሊተረጎም የሚችለው ሉላዊነት (ግሎባላዜሽን) የኢትዮጵያን ጥልቅ ጂኦግራፊያዊ ድንበሮች (deep geographic peripheries) በመድረስ ስር እየሰደደ ነው። ይህም የመሬት ኢንቨስትመንት መልክን በመያዝ ከ2000 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 2008) ጀምሮ የግብርና መሬት ፍላጎትን መሠረት ያደረገ እና በደቡቡ የዓለም ክፍል በስፋት የታየ ሂደት ሆኗል።ይህ አጭር የፖሊሲ ሀሳብ በምዕራብ ኢትዮጵያ የተደረጉ ጥናቶችን በመመርመርና በመተንተን እንደዚህ ያሉ የሉላዊነት ሂደቶች የህብረተሰቡንና የምርት ግንኙነቶችን በአካባቢያዊ ደረጃ እንደሚያደፈርስ የአካባቢውን ማህበረሰብም የሚጎዳ ሂደት እንደሆነ ያመለክታል።

ኢትዮጵያ እንደ ሌሎች ታዳጊ ሀገራት ሁሉ በሉላዊነት ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ብትሆንም፤የምትገኝበት የኢኮኖሚ እና የሀይል ደረጃ (የፖለቲካ ደህንነትን ጨምሮ) የጥግ ተሳታፊ (peripheral) አድርጓታል። የኢትዮጵያ በዚህ ሂደት መሳተፍ በማዕከል (core) እና በጥግ ተሳታፊ (peripheral) መካከል ያለውን ፍትሀዊ ያልሆነ ግንኙነት (የአሰራር ሂደት) ከማጠናከር ባሻገር የማዕከል ሀገራትን የሀብት ፍላጎት በጥግ ሀገራት ላይ ለማስረፅ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል።

ኢትዮጵያን በተከታታይ የመሩ ልሂቃን መሪዎች (elites) በምዕራብ ኢትዮጵያ ያሉ ቆላማ መሬቶችን ለሀገር ዕድገት ሊውሉ የሚችሉ ያልተነኩ የሀብት ምንጭ ናቸው ብለው ያምናሉ ቢባል ማጋነን አይሆንም። ከሀያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እነዚህን በዳር (peripheral) አካባቢዎች ያሉ ቆላማ መሬቶችን በሰውና በቴክኖሎጂ ቁጥጥር ስር የማዋል ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ የነበረ ነው።ይሁን እንጂ ይህ አመለካከት ለዘመናት የኖረውን የአካባቢውን ባህል፤ አኗኗርና የሀብት አጠቃቀም ዘዴ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ አይደለም። እነዚህ ቆላማ ቦታዎች ላይ የተደረጉ ውስን የልማት እንቅስቃሴዎችም ቢሆኑ ዕውን ሊሆኑ የቻሉት ከውጪ በተገኘ ካፒታልና በጊዜው በነበረው ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ምክንያት ነው።አሁን በነዚህ አካባቢዎች የሚታዩት የልማት እንቅስቃሴዎች በተለይም የሠፋፊ እርሻ ልማቶች ኢትዮጵያ በዓለምአቀፉ ሉላዊ ግንኙነት ውስጥ ባላት ቦታ ላይ የተመሠረቱ ሆነው ይገኛሉ።

## በኢትዮጵያ ሰፋፊ የእርሻ ኢንቨስትመንቶች ላይ ያሉ የቅርብ ተሞክሮች

በንጉሱ ዘመን በአዋሽ ተፋሰስ ዙሪያ የነበሩ የንግድ እርሻዎችና በደርግ ዘመን የነበሩ የመንግስት እርሻዎች ያልተሳኩበት ምክንያት ምን እንደሆነ በወጉ ሳይመረመርና በቂ ትምህርት ሳይወሰድበት በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ሠፋፊ የእርሻ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት ላይ ትኩረት አድርጓል። የኢህአዴግ መንግስት ይህንን ያደረገው በ2000ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ2008) የተከሰተውንና በእንግሊዝኛው

‹‹ሦስቱ ኤፎች›› (Triple F - Fuel, Food price and Financial) በመባል የሚታወቀውን የነዳጅ፣ የምግብ ዋጋ እና የገንዘብ ቀውስ እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም እና ቀውሱን ተከትሎ ለተከሰተው በታዳጊ አገሮች የሚታረስ መሬት ፍላጎት መሠረት በማድረግ ነበር:: በወቅቱ መንግስት ከሌሎች ተፎካካሪ ታዳጊ አገሮች በተለይም የአፍሪካ ሀገሮች የተሻለ ሆኖ ለመገኘት ርካሽ የመሬት ኪራይ ዋጋ፣ ነጻ የውሀ አቅርቦት እና ሌሎች ተመሳሳይ ድጋፎችን በማድረግ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል:: በዚህም ኢትዮጵያ "በአፍሪካ ለምግብ ኤክስፖርት የሚውል መሬት ወረራ ዋና ማዕከል" እስከመባል ደርሳለች:: ኢትዮጵያ እጅግ ርካሽ በተባለ የኪራይ ዋጋ መሬት በማቅረብ እና ሌሎች የማበረታቻ እርምጃዎችን በመውሰድ ይህንን ውድድር ለማሸነፍ ችላለች::

በአብዛኛው በሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት ንግድ ለመሳተፍ የመጡት ኢንቨስተሮች በከተሞች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ዲያስፖራዎች ሲሆኑ በጣም ጥቂት የውጪ ዜጎችም ነበሩበት:: ሆኖም ግን ለኪራይ ከቀረበው ጠቅላላ መሬት በአብዛኛው በውጪ ኢንቨስተሮች የተያዘ ነበር:: ለምሳሌም ያህል በጋምቤላ ክልላዊ መንግስት እስከ ሐምሌ 2004ዓ.ም ድረስ አራት መቶሀያ ከሚሆኑ መሬት በኪራይ ከወሰዱ ኢንቨስተሮች መካከል አስራ ሁለቱ ብቻ የውጭ ሀገር ዜጎች ናቸው:: በተቃራኒው እነዚህ ጥቂት የውጪ ሀገር ዜጎች ለኪራይ ከቀረበው አራት መቶ ሺህ ሔክታር መሬት መካከል ከግማሽ በላይ የሆነውን ወስደዋል::ለአብነትም ካራቱሪ የተባለው አንድ የውጪ ኢንቬስተር ብቻውን አንድ መቶ ሺህ ሔክታርመሬት ወስዶ ነበር::

ይሁን እንጂ በዓለም የተከሰተውን ቀውስ ተከትሎ እንደ መልካምዕድል የተቆጠረው ኢንቨስትመንት ለአካባቢው ማህበረሰብ መልካም ዜና አልነበረም::ይህ ሂደት በማህበረሰቡ ዘንድ ከመንግስት ጋር ለረጅም ጊዜ የቆየው መልካም ያልሆነ ግንኙነት ቀጣይ ሂደት ተደርጎ ከመወሰዱ ባሻገር የማህበረሰቡን ሀብት እንደመቀማት ተቆጥሯል:: በኢትዮጵያ መንግስት በኩል የአካባቢውን ማህበረሰብ እንደ እንቅፋት በመውሰድ ‹‹በፈቃድኝነት›› ላይ በተመሠረተ የሠፈራ ፕሮግራም ነዋሪውን ከአካባቢው ዞር ለማድረግ (ለማስወገድ) ጥረት ተደርጓል:: የጋምቤላና የቤኒሻጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስታት በመጀመሪያው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ከ2002-2007) መንግስት ለኢንቨስተሮች ሊያስተላልፍ ካቀደው 3.3 ሚሊዮን ሔክታር መሬት ወስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው መሬት ለኪራይ ያቀረቡ ክልሎች ነበሩ::በተጨማሪም በእነዚህ ቦታዎች የሚኖሩትን የገጠር ማህበረሰብ በሙሉ በሌላ አካባቢ ለማስፈር ዕቅድ ተይዞ ነበር:: ሆኖም ግን ሂደቱ በበቂ ሁኔታ ከአካባቢው ማህበረስብ ጋር በምክክር ባለመደረጉ በማህበረሰቡ ዘንድ ቅራኔ እንዲፈጠር፣ በመንግስትም ላይ ዕምነት እንዳይኖርና እና ተቃውሞም (resistance) እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል:: በመሆኑም መንግስት ያሰበውን ዕቅድ በስውርም ሆነ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ በማስገደድ ለማስፈጸም ጥረት አድርጓል::

ሰፋፊ የእርሻ ኢንቨስትመንት እና የልማታዊ መንግስት ትርክት

የጥግ ተሳታፊ (peripheral) በሆኑት የምዕራብ ኢትየጵያ ቆላማ ቦታዎች የመሬት ስምምነቶችና የሰፈራ እንቅስቃሴዎች ጎልተው የሚታዩ የልማታዊ መንግስት ትግበራ ውጤቶች ነበሩ:: ሆኖም ለትግበራው ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ድጋፍና የፋይናንስ ኢንቨስትመንት፤እንዲሁም አመቺ ዓለምዓቀፋዊ ሁኔታ ቢኖርም ጥረቱ በአሳዛኝ ሁኔታ ውድቅ ሆኗል፤ የመንግስት ግምገማም ይህንን ውድቀት አመላክቷል:: ያልተሳካበትን ዋና መሠረታዊ ምክንያት ለመረዳት የተለያዩ ሁኔታዎች ማየት ይገባል:: ከነዚህም መካከል ሙስና፣ከመሠረተ ልማት ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ በመንግስት በኩል ያለው ክትትልና ድጋፍ መድከም፤ እንዲሁም ዕቅዶቹ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ማጣታቸው በዋናነት ይጠቀሳሉ::

ማህበረሰቡም በግልጽም ሆነ በድብቅ በተለያየ መንገድ ተቃውሞውን ሲገልጽ ቆይቷል::እነዚህ ተቃሞዎች በተለይ ለሠፈራ መርሀ-ግብሩ አለመሳካት ዋና ምክንያት ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ:: የእርሻ ኢንቨስትመንት በስጋት የተሞላ እንዲሁም ተጨማሪ ወጪ የሚያስከፍል እንደሆነ አመላካችና ለውድቀቱም ምክንያት እንደሆነም ያመለክታል::በአካባቢው ማህበረሰብ ላይም ቢሆን ሁኔታው ያስከተለው ጉዳት ቀላል የሚባል አይደለም:: የሰዎችን ሞት፣ ስደት፣ አስገዳጅ የቦታ ዝውውርንና የምግብ ደህንነት ማጣት ችግሮችን አስከትሏል::

ከነዚህ ልምዶች የተገኘው ትምህርት መንግስት መሬትንና የውሀ ሀብትን ጨምሮ በምዕራባዊው ቆላማ አካባቢዎች ውስጥ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች በተገቢ ሁኔታ የማስተዳደር እና ሀላፊነቱን በሚገባ መወጣት

እንዳለበት የሚያሳስቡ ናቸው:: ይህ መሆን ያለበት ከታች ለተዘረዘሩት ምክንያቶች ነው፡-

1ኛ) በቂ የሆነ የፖሊሲ ድጋፍ በሌለበት ሁኔታ ታች ላለው የህብረተሰብ ክፍል ማህበራዊ አገልግሎቶችን በበቂና በተሟላ ሁኔታ ለማድረስ ያለው ዕድል ጠባብ ይሆናል::

2ኛ) አሁን በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚታየውን የምግብ ዋስትና ችግር፣ የምግብ ዋጋ መናር እና ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ ስራ አጥነት (በተያያዥ የሚከሰቱ ግጭቶችንና ህገ-ወጥ ስደትን) ችግሮችን ግምት ውስጥ በማስገባት መንግስት በአካባቢው ያሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች በመጠቀም በቂ የምግብ ሰብል የሚመረትበትንና የምግብ ዋስትና የሚረጋገጥበትን፤ እንዲሁም የስራ ዕድሎች የሚፈጠሩበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሀላፊነት አለበት::

3ኛ) በምዕራብ ኢትዮጵያ ቆላማ ቦታዎች በሚኖረው ማህበረሰብ አመለካከት ህብረተሰቡ አሁን በሚታየው ሁኔታ ከፍተኛ ተፅዕኖና ጉዳት እንደደረሰበት ይታሰባል::ሁኔታው በዚህ ከቀጠለና ለችግሮቹ በጊዜ መፍትሔ ካልተሰጠ ጉዳቱ እየጨመረ፣ ችግሮቹ እየተወሳሰቡና ጫናው እየሰፋ እንደሚሄድ ይታመናል:: በመሆኑም የፖሊሲ አውጪዎች ትኩረት አሁን ያለውን ሀገር አቀፍ ችግር በመቅረፍ ላይ ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው ማህበረሰብ ፍላጎት ምላሽ በመስጠትም ላይም ሊሆን ይገባል::

በምዕራብ ኢትዮጵያ ቆላማ ቦታዎች የሚደረግ የልማት እንቅስቃሴ ዘለቄታዊነትና ውጤታማነት የሚወሰነው የአካባቢው ማህበረሰብን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ሲቻልና በፖሊሲ ማውጣት ስርዓት ሂደት ውስጥም በመንግስትና በማህበረሰቡመካከል ያለውን መልካም ያልሆነ ግንኙነት መለወጥ ሲቻል ብቻ ነው:: ለዘመናት ሀገሪቷን የመሯት መንግስታት በምዕራባዊ ቆላማ አካባቢዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦችን እንደ ኢ-ምክንያታዊና ኋላቀር ይመለካታሉ::በዚህ ሳቢያ በሚደረጉት ‹‹የልማት ጥረቶች›› ውስጥ ህብረተሰቡን የማማከር እና ፍላጎቱን የማዳመጥ ጥረት ካለመደረጉ በላይ መንግስታት የህዝቡን የአኗኗር ሁኔታና የኑሮ ዘይቤ ካለፍላጎቱ ለመቀየር ሲጥሩ ይስተዋላል:: ይህ አመለካከት ሊቀየር ይገባዋል:: የአካባቢው ማህበረሰብ ብቃት፣ ችሎታ እና ሚዛናዊ አመለካከት እንዳለው ግንዛቤ ተወስዶ ተገቢውን ትኩረት እና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል:: ማህበራዊና ባህላዊ የሆነው የችግሩ ዘርፍ ትኩረት እስካልተሰጠው ድረስ የልማት ስራዎች ያልተሳኩበትን ቴክኖሎጂያዊ፣ አቅማዊ እና መሠረተ-ልማታዊ ችግሮች ላይ ብቻ ያተኮረ መፍትሔ ለመስጠት መጣር ተፈላጊውን ሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና አካባቢያዊ መሻሻል ሊያመጣ አይችልም::

## የፖሊሲ ምክረ- ሀሳቦች

ኢትዮጵያ በሉላዊነት (globalization) ሂደት ውስጥ ካላት የጥግ ተሳታፊነት (peripheral) አንፃር መንዳቷ አይቀሬ ነው:: በመሆኑም አሉታዊ ተፅዕኖዎችን በመቋቋም አዎንታዊ ዕድሎችን መጠቀም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው:: የሀገር ኢኮኖሚን ማሳደግ፣ የአገልግሎት አሰጣጥን የተሻለ ማድረግ እና የአካባቢ ማህበረሰብን አኗኗር ማሻሻል የሚቻለው በሀገር ውስጥ ለሚታዩት የፖለቲካና ኢኮኖሚ ልዩነቶች መፍትሔ መስጠት፣ እንዲሁም ሉላዊነት የፈጠረውን ዕድል (መሬትን ማከራየትን ጨምሮ) በተገቢው ሁኔታ መጠቀም ሲቻል ነው:: ይህንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሦስት የፖሊሲ ምክረ-ሀሳቦች ተሰንዝረዋል::

1. የአካባቢውን ማህበረሰብ ፍላጎት ማዕከል ያደረገ የልማት ፖሊሲና ትግበራት መዘርጋት

ከዚህ ቀደም በነበረው አሰራር የእርሻ መሬቶች ላይ በሚደረግ የልማት ዕቅድ ውስጥ የአካባቢው ማህበረሰብ ፍላጎቶች ችላ ይባላሉ፤ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ግምት ይሰጣቸዋል:: ህብረተሰቡ መንግስት ከማዕከል ከሚጭንበት የፖሊሲ ሀሳብና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ጋር ራሱን እንዲያስማማ ይጠበቅበት ነበር::

ከዚህ ቀደም ባለው አሰራር ውሳኔ የተሰጠውን ሀሳብ ወደ ማህበረሰቡ ይዞ ሄዶ የማሳመን እንጂ ሀሳቡን በቅድሚያ ይዞ በመሄድ እውነተኛ ምክክር ማካሄድ፣ ሀሳቡን የማበልፀግና የአካባቢውን ማህበረሰብ ይሁንታና ፈቃድ የማግኘት አሰራር አልነበረም:: በዚህም ምክንያት ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች በደህንነት ስጋት እንዲዋጡ ሆነዋል:: ለዚህ ችግር ዋናው ምክንያት ከአካባቢው ማህበረሰብ ይልቅ መንግስትና ገዢው ፓርቲ የተሻለ ያውቃሉ የሚል የተሳሳተ ጭፍን አመለካከት በመስፈኑ ነው:: እውነተኛ የሆነ ምክክርና አብሮ መስራት እንዲኖር ከተፈለገ ይህ አይነት አመለካከት ሊስተካከል ይገባዋል:: ከዚህ በተጨማሪም ከዚህ ቀደም በነበረው አካሄድ መንግስት የመሬትን ኢኮኖሚያዊ ዋጋ ብቻ በመመልከት ለማህበረሰቡ ግድ የሚሰጡ ሌሎች ጉዳዮችን ችላ ሲል ይስተዋል ነበር::እውነታው ግን እንደ ምዕራብ ቆላማ ቦታዎች ነዋሪዎች እይታ መሬት ከኢኮኖሚያዊ ዋጋው ባለፈ ከማንነትና ከማህበረሰብ አደረጃጀት ጋር

የተቆራኘ በመሆኑመንግስት ይህንን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ፖሊሲ ሊቀርፅ ይገባል፡፡

2. ሁሉን አቀፍ የሆነ የረጅም ጊዜ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ማውጣት

ያለፉት ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት በአካባቢዎቹ የተተገበሩት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ዝርዝር፣ ሁለገብና፣ ሁሉን አቀፍ ዕቅድን ተከትለው የተተገበሩ አልነበሩም፡፡ፕሮጀክቶች በተበታተነ ሁኔታ ሲተገበሩ እንደነበረ ታይቷል፡፡ ለምሳሌም ያህል የጊቤ ሦስት ግድብ በመገደብ ላይ እያለ ትላልቅ የስኳር እርሻዎችን በታችኛው የኦሞ ሸለቆ ለማቋቋም ዕቅድ እንዳለ ለህዝቡ ይፋ አልተደረገም ነበር፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ በጋምቤላ ክልልም የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድብ ግንባታ ጥናትና ተያያዥነት ያላቸው ዕቅዶች የመጡት መሬትን ለእርሻ ኢንቨስትመንት የመስጠቱ ሂደት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ እንደነበር አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ጥናት በአሳታፊ ሁኔታ ተካሂዶ ቢሆን ኖሮ ለሁሉም የመሬት ንጣፎች (parcels) አጠቃቀም አይነቶችን ለይቶ መመደብ ይቻል ነበር፡፡ይህም እንደ ብዝሀ-ሕይወት ጥበቃ፣ አካባቢ ጥበቃ እና ሰፊ የግብርና ኢንቬስትመንት የመሳሰሉ ተወዳዳሪ ፍላጎቶችን ለማጣጣም ይረዳል፡፡ከዚህ በተጨማሪ በተፋሰስ ወይም በክልል ደረጃ የሚካሄዱ ዝርዝር የመሬት አጠቃቀም ጥናቶች ምንም እንኳን ውድ እና ጊዜ የሚወስዱ ቢሆኑም፤ ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንቶች የሚገጥሟቸውን በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተግዳሮቶች ለመከላከል ይረዳሉ፡፡

3. በምርት ላይ ዕሴትን በቦታው መጨመር

በምዕራብ ቆላማ ቦታዎች ላይ የሚመረቱ እንደ ጥጥ ያሉ የግብርና ግብዓቶችን የሚጠቀሙ አምራች ኢንዱስትሪዎችን የሚገኙት ከማምረቻ አካባቢዎች በጣም ርቀው ነው፡፡ ይህም በአብዛኛው ከማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መሠረተ-ልማታዊ ችግሮች ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ቢሆንም ሁኔታው በዚሁ እንዲቀጥል ማድረግ በደጋ እና በቆላ የሀገሪቱ ክፍሎች መካከል ያሉትን ልዩነቶችና መበላለጦች እንዲቀጥሉ መፍቀድ ይሆናል፡፡

በቦታው ላይ ዕሴት መጨመር እና የግብርና-ኢንዱስትሪያላይዜሽንን ማስፋፋት ከአካባቢዎቹ የሚገኙ ከእርሻ የሚገኙ ጥቅሞች ወደ ደጋማ አካባቢዎች "እንዳይተላለፉ" ከመከላከሉ በላይ በቆላማ አካባቢዎች ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ያጠናክራል፡፡ ምርቱ በሚመረትባቸው አካባቢዎች ላይ የሚደረግ ዕሴት መጨመር ከግብርና ውጪ ባሉ ዘርፎች ላይ ተጠቃሚነትን በማሳደግ የጥግ ተሳታፊ የሆኑ ቆላማ ቦታዎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፡፡ይሁን እንጂ ይህ ሂደት በአካባቢ ደረጃ የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚያመጣ ቢሆንም ይህንን ተከትሎ ወደ ቆላማ ምዕራብ ቦታዎች በስፋት ሊደረግ የሚችለው ያልተገራ የሥራ ፍልሰት ማህበራዊ ግጭትን ሊያስከትል ስለሚችል መቆጣጠር ይገባል፡፡

በፋና ገብረሰንበት

ምንጭ፡ ፋና ገብረሰንበት (2013) ሉላዊነት፣ ሰፋፊ የእርሻ ኢንቨስትመንቶች እና የአካባቢው ነዋሪዎች ምላሽ በምዕራብ ኢትዮጵያ

ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳብ የታተመው የኦፐን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) የገንዘብ ድጋፍ ነው በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን፣የድርጅቱን አጋሮችና የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን የኦፐን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል፡፡

§§ አድራሻ፡- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) §§ ፖ.ሣ.ቁ.፡- 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

§§ ስልክ፡- 011154 56 05/06 §§ ፋክስ፡- 011154 56 07 §§ ኢሜል፡- fss@ethionet.et §§ ድረ-ገጽ፡- www.fssethiopia.org